ቅጽ 9 ቁጥር 10 ታህሳስ 1996

# ዜና አመዝኮ

**አ**
የአደጋ
**መ**
መከላከልና
**ዝ**
ዝግጁነት
**ኮ**
ኮሚሽን

## በዚህ እትም የውስጥ ገፆች...

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያለው የድርቅ ሁኔታ መሻሻሉ ተገለፀ
- ለ176 ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጠ
- ከ15.2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተከፋፈለ
- በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን ከብር 389 ሺህ በላይ ተለገሠ

*ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትንየሚዘግብ ወርሃ ልሣን ነው።*

*በአመዝኮ የሕዝብ ግንኙነት የተዘጋጀ*
☎ 52 92 59
52 92 62
✉ 5686 ፋክስ 514788
**web.http// www. dppc.gov.et**

# በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያለው የድርቅ ሁኔታ መሻሻሉ ተገለፀ

በሱማሌ ክልል ፣ በኦሮሚያ ቦረና ዞንና ደቡብ ሕዝቦች ደቡብ ኦሞ ዞን አርብቶ አደር አካባቢዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅት ተከትሎ በተካሔደው የአጠቃላይ ሁኔታዎች ግምገማ ውጤት በጥቅምትና ህዳር ወራት ይጠበቅ የነበረው ዝናብ በመዘግየቱና አነስተኛ በመሆኑ ተፈጥሮ ከነበረው ከፍተኛ ስጋት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ የተሻለ መሆኑን አመለከተ::

ከአመዝኮ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ ከብሄራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት ፣ ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት ፣ ከዓለም ምግብ ኘሮግራም ፣ ከአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጀት ፣ ከኬር ኢትዮጵያ እና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከክልል አመዝ ቢሮዎች ከተውጣጡ ባለሙያዎች የተዋቀሩት ስድስት አጥኚ ቡድኖች የጥናታቸውን ውጤት ፣ ታህሳስ 27 ቀን 1996 ዓ.ም በኮሚሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት በነዚህ አካባቢዎች አጠቃላይ የዝናቡ ሁኔታ ሲታይ በጥቅምትና ህዳር ወራት የነበረው ዝናብ ሙሉ በሙሉ አጥጋቢ ባይሆንም ወትሮ ባልተለመደ ሁኔታ በታህሳስ ወር የተገኘው ከፍተኛ ዝናብ በአብዛኛዎቹ በአካባቢዎች የግጦሽና የውሀ ችግር አቃልሏል::

በስድስት ቡድኖች ተከፍለው በሱማሌ ክልል ፣ በኦሮሚያ ቦረና ዞንና በደቡብ ህዝቦች ደቡብ ኦሞ ዞን ከታህሳስ 2 – 25/1996 ዓ.ም ያካሄዱትን የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅት አጠቃላይ ሁኔታ ግምገማ ውጤት በየቡድን ሪፖርቶቻቸው እንዳመለከቱት በሱማሌ ክልል ጅጅጋ እና ሽኒሌ ዞኖች ያሉ ነዋሪዎች በእንስሳት ዕርባታ ብቻ የሚተዳደሩ እና የእንስሳት እርባታ እና ግብርናን በማጣመር የሚተዳደሩ ተብለው የሚከፈሉ ናቸው:: በጅጅጋ ዞን አርሶ አደር በሆኑት ወረዳዎች የወቅቱ ዝናብ ለግጦሽ ፣ ለውሀና እንደ ገብስና ስንዴ ለመሳሰሉት የአጭር ጊዜ ሰብሎች በቂ ሊባል የሚቻል ቢሆንም አብዛኛው የዞኑ አርሶ አደር የሚያመርታቸው እንደ ማሽላና በቆሎ የመሳሰሉ የረጅም ጊዜ ሰብሎች በዝናቡ እጥረት ሳቢያ ውጤት አልባ መሆናቸው የተመለከተ ሲሆን በዚሁ ዞን ሙሉ በሙሉ አርብቶ አደር በሆነው የሀርሸን ወረዳ የወቅቱ ዝናብ ባለመጣሉ የውሀና የግጦሽ እጥረት የሚታይ መሆኑን በዞኑ የተደረገው ጥናት ወጤት ሪፖርት ያመለክታል::

በሌላ በኩልም በሸኒሌ ዞን በነበረው የዝናብ ሁኔታ በዞኑ አርሶ አደር ወረዳዎች የሰብል ምርት አለመገኘቱን ያብራራው የጥናት ወጤት በዞኑ የግጦሽና የውሀ ሁኔታም በሚፈለገው መጠን ባይሆንም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዳልደረሰም ጠቁሟል:: ይሁን እንጂ ቀጣይ በአካባቢው የሚጠበቀው ''ጉ'' እየተባለ የሚጠራው ዝናብ አጣጣል ከተስተካከለ የተሻለ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ሊታይ እንደሚችል በሪፖርቱ ተመልክቷል:: በጅጅጋና በሽኒሌ ዞኖች ማጠቃለያ ሪፖርታቸው በሁለቱ ዞኖች የአብዛኛው ነዋሪ የገቢ ምንጭ በግብርናና በእንስሳት እርባታ ላይ በመመሥረቱ የግብርና ምርቱ ውጤት አልባነት በሕዝቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ለነዚህ ወገኖችም የምግብ ዕርዳታ እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል::

በሌላ በኩልም በዋርዴር ፣ ጎዴ ፣ ደገሀቡር፣ ቆራሔ እና ፊቅ ዞኖች ግምገማቸውን ያካሔዱ ቡድኖችም በነዚህ ዞኖች ያለው ሁኔታ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው ቢባልም በወቅቱ የተጠበቀው ዝናብ ሥርጭትና መጠን አነስተኛነት የተነሳ በተለይ በዋርዴር ፣ ቆራሔ እና ፊቅ ዞኖች ለግጦሽና ለውሀ እጥረት መከሰት ዓይነተኛ ምክንያት እንደሆነ በስፋት አብራርተዋል::

በአፍዴር ዞን ከምዕራብ ኢሚ ወረዳ በስተቀር በሌሎች ወረዳዎች ያለው የውሃና የግጦሽ ሁኔታ ጥሩ መሆኑን ፣ በምዕራብ ኢሚ ወረዳ ግን ሁለተኛው የወቅቱ ዝናብ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ ባለመጣሉ ሳቢያ የግጦሽና የውሀ እጥረት መታየቱን ወደዞኑ የተሰማራው አጥኚ ቡድን አመልክቷል::

በአጠቃላይ በሱማሌ ክልል ካለፉት ዓመታት ድርቅ ጋር በተያያዙ ሁኔታዎችና በዚህ ዓመትም በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች በቀጠለው የዝናብ አለመስተካከል ሳቢያ ከሦስት እስከ ስድስት ወራት የምግብ ዕርዳታ እና የውሀ አቅርቦት የሚያስፈልጋቸው ወገኖች እንደሚኖሩ ፣ የተረጂዎቹ ቁጥር ካለፈው ዓመት ጋር ተቀራራቢ እንደሚሆን አጥኚ ቡድኖቹ ካቀረቧቸው የጋራ ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል::

በሌላ በኩልም በኦሮሚያ ቦረና ዞንና በደቡብ ህዝቦች ደቡብ ኦሞ ዞን የተሰማሩት አጥኚ ቡድኖች እንዳመለከቱት በነዚህ ሁለት ዞኖች የነበረው ሁለተኛ የወቅቱ ዝናብ አጥጋቢ ስለነበረ ሥር በሰደደ ድህነትና በጥሪት መሟጠጥ ሳቢያ የቅርብ ክትትል ክማያ ስፈልጋቸው የተወሰኑ የህብረተ ሰቡ ክፍሎች በስተቀር በሁለቱ ዞኖች ያለው የምግብ ዋስትና በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል::

# ለ176 ሠራተኞች ሥልጠና መስጠቱ ተገለፀ

የኮሚሽኑ የሥራ አመራርና ማሰልጠኛ አገልግሎት በ1995/96 ዓ.ም በአጠቃላይ በ23 ዓይነት የሥልጠና ኘሮግራሞች ለ176 ሠራተኞች የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና የተሰጠ መሆኑን ገለፀ፡፡

ከአገልግሎቱ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተውም የተሰጡት የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ፀሐፊዎችን ፣ ቴክኒሻኖችን ፣ ኤክስኘርቶችንና ሌሎች ባለሙያዎችን ያካተቱ ሲሆን ፣ ሥልጠና ከወሰዱት ሠራተኞች መካከልም 87 ሴቶች 89 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ ከተሰጡት 23 ሥልጠናዎች 21 በሀገር ውስጥ ቀሪዎቹ 2ቱ ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጡ መሆናቸውን ያመለከተው አገልግሎቱ የተሰጡት ሥልጠናዎች በአጠቃላይ ሲገመገሙ ለኮሚሽኑ አቅም ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸውን አክሎ ገልጿል፡፡ አገልግሎቱ አያይዞም እነዚህ በአገልግሎቱ በኩል የተሰጡ ሥልጠናዎች በተመድ ልዩ ልዩ አካላት፣ በዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ፣ በመያ ዶችና በቀጥታ የሥራ ግንኙነት በሌሎች አካላት ወጪ የተሰጡ ሌሎች የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠናዎችን አይጨምሩም፡፡

በ1995/96 ዓ.ም ለሠራተኞች ለተሰጡት 21 ዓይነት የሀገር ውስጥ ሥልጠናዎች ብር 163 ሺህ 876 ወጪ በኮሚሽኑ መሸፈኑ ታውቋል፡፡ በውጭ ሀገር ለተካሄዱት ሁለት ሥልጠናዎች ደግሞ የኔዘርላንድ መንግሥትና የዓለም ምግብ ኘሮግራም ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ወጪ የሸፈኑ መሆኑን የገለጸው አገልግሎቱ በቀጣይም በ1996 በጀት ዓመት 19 ዓይነት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ኘሮ ግራሞች በቡድንና በተናጠል ለሠራ ተኞች ለመሥጠት ማቀዱንም አስታ ውቋል፡፡

አገልግሎቱ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናን በተመለከተ የኮሚሽኑ የሥራ ዘርፎች በበጀት አስደግፈው የሚያቀርቧቸውን የሥልጠና ጥያቄዎች ከሥልጠና ዋና ዓላማና መርሆ ፣ ከተመደቡበት የሥራ መደብ አንጻር የብቃት ክፍተት የሚታይባቸውና ሥልጠና የሚያስፈ ልጋቸውን ሠራተኞች ለይተው ሲያቀርቡ ሥልጠናው የሚገኝበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች አስረድቷል፡፡ ከዚሁ ጋርም የሥልጠና ቅደም ተከተል ከማስቀመጥ እንዲሁም አሠልጣኝ ድርጅቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ከማመላከት አNያ በመቃኘት ሲያቀርቡ አገልግሎቱ ባለው የማስፈጸም አቅም በመንቀሳቀስ የሥልጠና ጥያቄዎችን ለማሟላት ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

# ከ15.2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተከፋፈለ

❖ ለታህሳስ ወር ከ407 ሺህ ኩንታል በላይ ተመድቧል

ባለፈው ዓመት ተከስቶ በነበረው ደርቅ ሳቢያ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ወገኖቻችንን ለመደገፍ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ከጥር እስከ ታህሳስ ባለው ጊዜ ውስጥ በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች በጠቅላላው 15 ሚሊዮን 270 ሺህ 662.7 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ የተከፋፈለ መሆኑን ከኮሚሽኑ የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

ከዚሁ በዓመቱ ውስጥ ከተመደበውና ለተረጂዎች ከተከፋፈለው የምግብ ዕርዳታ ወስጥ 7 ሚሊዮን 816 ሺህ 107 ኩንታል በአመዝኮ ቀሪው 7 ሚሊዮን 454 ሺህ 555.4 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የቀረበ መሆኑን ለማቅ ተችሏል:

ይኸው የምግብ ዕርዳታ በትግራይ ፣ አፋር ፣ አማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ ሱማሌ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ ደቡብ ሕዝቦች ፣ ድሬደዋ ፣ ሐረሪና ጋምቤላ ክልሎች ለሚገኙ 13.2 ሚሊዮን ተረጂዎች የተከፋፈለ ነው:: ለየክልሎቹ የሚመደበው ዕርዳታም በየክልሎቹ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት በቅደም ተከተል ተመድቦ መከፋፈሉ ተመልክቷል:: በዚሁ መሠረት በተጠናቀቀው የአውሮፓውያኑ 2003 ዓ.ም ውስጥ ከተከፋፈለው የምግብ ዕርደታ ውስጥ ለኦሮሚያ 4 ሚሊዮን 345 ሺህ 309 ኩንታል ፣ ለአማራ 3 ሚሊዮን 346 ሺህ 389 ኩንታል ፣ ለትግራይ 2 ሚሊዮን 557 ሺህ 513.1 ኩንታል ፣ ለደቡብ ሕዝቦች 1 ሚሊዮን 890 ሺህ 630.7 ኩንታል ፣ ለሱማሌ 1 ሚሊዮን 583 ሺህ 947.4 ኩንታል ፣ ለአፋር 1 ሚሊዮን 329 ሺህ 595.9 ኩንታል ፣ ለድሬደዋ 117 ሺህ 247.6 ኩንታል ፣ ለጋምቤላ 58 ሺህ 335 ኩንታል ፣ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ 21 ሺህ 330 ኩንታል እና ለሐረሪ 20 ሺህ 365 ኩንታል ተመድቦ እስከ ህዳር ወር ያለው ተጓጉዞ ለተረጂዎች መከፋፈሉ ታውቋል::

በአጠቃላይ ለዓመቱ በየክልሎች ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ከተላከው የምግብ ዕርዳታ ውስጥም 407 ሺህ 711.5 ኩንታል ለአውሮፓውያን ዓመት የመጨረሻ ወር ለሆነውና በእኛ የታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም የሚሆን ቀለብ እንደሆነና አብዛኛው ለተረጂዎች መከፋፈሉም ከዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ለወሩ ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥም 266 ሺህ 907.5 ኩንታል በአመዝኮ ቀሪው 140 ሺህ 804 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ ነው::

በየክልሎች ካለው ችግር ስፋትና ጥልቀት አኳያ ከተላከው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ 181 ሺህ 538 ኩንታል ፣ ለአፋር 123 ሺህ 511 ኩንታል ፣ ለደቡብ ህዝቦች 58 ሺህ 489 ኩንታል፣ ለኦሮሚያ 22 ሺህ 249 ኩንታል ፣ ለአማራ 19 ሺህ 299.5 ኩንታል እና ለጋምቤላ 2 ሺህ 625 ኩንታል የተመደበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

## በድርቁ ለተጎዱ ወገኖቻችን ከብር 389 ሺህ በላይ ተለገሠ

በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ወገኖቻችንን ለመደገፍ ከሀገር ውስጥ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚያደርጉት የገንዘብ ዕርዳታ እንደቀጠለ ሲሆን በዚሁ መሠረት ከህዳር ወር 1996 ዓ.ም መጨረሻ እስከ ታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ 397 ሺህ 840 ብር ከ71 ሳንቲም በኮሚሽኑ የፋይናንስ አገልግሎት በኩል ገቢ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል::

ዕርዳታውን ከለገሡት መካከልም የተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ ማህበራት፣ ዕድሮች ፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ይገኙባቸዋል::

በአጠቃላይ ከድርቁ መከሰት ማግስት ጀምሮ እስከ ታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ በድርቁ ሳቢያ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ ከሀገር ውስጥ የተለገሠው የገንዘብ ዕርዳታ በድምሩ ከ102 ሚሊዮን ብር በላይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 89 ሚሊዮን 677 ሺህ 985 ብር ከ21 ሳንቲም ከሀገር ውስጥ በማዕከልና በክልሎች በጥሬ ገንዘብ የተለገሠ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳ□ች ደግሞ 469 ሺህ 190 ከ53 የአሜሪንን ዶላር ፣ 42 ሺህ 450 የስዊስ ፍራንክ ፣ 90 ሺህ 574.34 የሮ እና 8 ሚሊዮን 104 ሺህ 200 የጅቡቲ ፍራንክ በጥሬ ገንዘብ የተለገሰ ሲሆን ፣ ቀሪው ደግሞ ግምታቸው ብር 4 ሚሊዮን በሚሆን የቁሳቁስ ዕርዳታ የተለገሠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::